የሰበር መዝገብ 65427

ቀን 15/9/2003

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ሜታ አቦ ቢራ አ/ማ ነገረ ፈጅ አቶ ሰለሞን ዘውዴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ወ/መድህን ቢረዳ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የአሁኑ ተጠሪ ለሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ በተከሳሽ ድርጅት /የአሁን አመልካች/ በዩቲሊቲ ክፍል ሃላፊ ሆኜ ስሰራ ቆይቼ ማያዝያ 26 ቀን 2001 ዓ.ም በሥር ላይ በደረሰብኝ አደገ በህክምና የተረጋገጠ 7% ጉዳት የደረሰብኝ ስሆን ተከሳሽ ክፍያ የፈፀመልኝ ካደረሰብኝ ጉዳት ባነሰ በመሆኑ ቀሪውን ገንዘብ ከነ ወለዱ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽም በሰጠው መልስ ተከሳሽ በገባው የመድን ዋስትና መሰረት ለከሳሽ የሚገባውን የካሣ ገንዘብ ከፍሏል፡፡ ስለሆነም ቀሪ የሚከፈለው ካሣ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በበኩሉ ወደ ክሱ ጣልቃ በመግባት የተከራከረ ሲሆን የሥር ተከሳሽ በገባው የመድን ሽፋን መሠረት ክፍያ መፈፀሙን ገልጿል፡፡ የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/2/ መሠረት ለከሣሽ ተገቢውን ካሣ የከፈለ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

የሥር ከሣሽም በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብይ መልስ ሰጪው ቀደም ሲል ከከፈለኝ ገንዘብ ብር 7500 በተጨማሪ ብር 8649 ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረብኩትን ክስ የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ከፍተኛ ፍ/ቤትም የመልስ ሰጪዎችን መልስ ከቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ጋር ከመረመረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/1/ ድንጋጌ መሠረት ለሠራተኛ የሚከፈል የጉዳት ካሣ አሠሪው በገባበት የመድን ዋስትና ተፈፃሚ ይሆናል ተብሎ የተገለፀው የመንግስት ሠራተኞችን የሚመለከት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በ1ኛ መልስ ሰጪ /የአሁን አመልካች/ እና 2ኛ መልስ ሰጪ /የኢት/መድን ድርጅት/ መካከል የተደረገው የመድን ሽፋን ውል ህግ ሆኖ የሚገዛው ሁለቱን ተዋዋይ ወገኖችን

እንጂ ይግባኝ ባይ /ያሁን ተጠሪን/ የውሉ ተገዢ ለማድረግ ሙሉ በሙሉ የሚያስገድድ አይደለም በማለት 1ኛ መልስ ሰጪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ መሠረት ከደረሰው የአካል ጉዳት ጋር ተያይዞ ቀሪ የካሣ ክፍያ ብር 8649 የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት ፈርዷል፡፡

በሥር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም አመልካች የመንግስት የልማት ድርጅት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ የመንግስት ሠራተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አሰሪው ካሣ መክፈል ያለበት በአዋጅ አንቀጽ 109/1/ መሠረት አሰሪው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ መሠረት ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም አመልካች በገባው የመድን ዋስትና መሠረት ከሚገባው ካሣ በላይ ለተጠሪው ከፍሏል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ን ለውሣኔው መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ አንቀጽ ከ109/2/ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው በጡረታ ህግ ላልተሸፈኑ ሠራተኞች አሰሪው በአንድጊዜ ስለሚከፍለው ካሣ ሲሆን ተጠሪ ግን የጡረታ ሽፋን ያለውና እንደማንኛውም ሠራተኛ ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት የሚከበርለት ነው፡፡ ስለሆነም የስር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳይ በተጠቀሰው ህግ አንቀጽ 109/3/ለ/ ሥር የሚሸፈን ነው በማለት ተጠሪው በተጨማሪነት እንዲከፈለው የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ያለአግባብ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ አመልካች ለሠራተኛው የገባው የመድን ዋስትና የሚያስገኘው ጥቅም አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ ለሠራተኛው የሚሰጠው ጥቅም ያነሰ ነው፡፡ የህብረት ስምምነቱም የካሣ ክፍያን አስመልክቶ ለሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ካስቀመጠው ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ተፈፃሚነት የለውም ተጠሪም እንዲከፍለኝ የጠየቅኩት የህብረት ስምምነቱ ያስቀረብኝን ጥቅም በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ሲል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው ብሏል፡፡

አመልካችም ለተጠሪ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን እኛም አመልካች በቀሪነት የሚፈለግበትን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለተያዘውን ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት ስለ ጉዳት ካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109 የተደነገገውን መመልከት ተገቢነት ያለው ነው፡፡ የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 109/1/ የሚናገረው በመንግስት ድርጅቶች ሠራተኞች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ካሣ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ሲሆን አከፋፈሉም አሠሪው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ መሠረት መሆኑን ይገልፃል፡፡ አንቀጽ 109/2/ ደግሞ ተፈፃሚ የሚሆነው በጡረታ ህግ ላልተሸፈኑ ሠራተኞች ሲሆን የጉዳት ካሣውም የሚከፈለው በጡረታ ህግ መሠረት ሳይሆን በአንድ ጊዜ ክፍያ ነው፡፡ የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ ከንዑስ ቁጥር 2 ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ስለ ጉዳት ካሣው መጠን ስሌት የሚናገር ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በደንብ ቁጥር 64/85 የተቋቋመ ሲሆን ተጠሪውም የመንግስት ሠራተኞች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪው የደረሰበት ጉዳት 7% እንደመሆኑ መጠን መደበኛ ሥራውን እያከናወነ ያለና በጡረታ ህግ የተሸፈነና

ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አበል ጭምር የሚያገኝ መሆኑን አመልካች ያስረዳ ሲሆን ተጠሪው ግን ይህን በሚያስተባብል መልኩ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡

ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪው ክርክር መወሰን ያለበት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደጠቀሰው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ ሳይሆን በአንቀጽ 109/1/ መሠረት ነው፡፡ በዚህ በተጠቀሰው አንቀጽ ማለትም 109/1/ መሠረት አንድ የመንግስት ድርጅት በሰራተኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የሚከፍለው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ ሲሆን ይህ ሊቀየር የሚችለው አሠሪውና ሠራተኛው በህብረት ስምምነታቸው በተቃራኒ ተስማምተው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በህብረት ስምምነት በተቃራኒ የተወሰነ ወይም የተደረገ ስምምነት ስለመኖር በሥር ፍ/ቤት በአስረጂነት የቀረበ ነገር የለም፡፡

አመልካችም የጉዳት ካሣውን ገንዘብ የከፈለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/1/ መሠረት ለተጠሪው በገባለት የመድን ዋስትና ሲሆን የዋስትና ሽፋኑም ብር 7500 በመሆኑና ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪው መክፈሉን ገልጿል፡፡ በአንቀፁ የጉዳት ካሣው አሰሪው በገባበት የመድን ዋስትና ሊሆን እንደሚችል ከተደነገገው በተጨማሪ በአመልካች እና በሜታ አቦ ቢራ አክስዮን ማህበር መሠረታዊ የሠራተኞች ማህበር መካከል በ2000 ዓ.ም በተደረገው የህብረት ስምምነት አንቀጽ 32 ድርጅቱ /አመልካች/ ለማንኛውም ሰራተኛ በሥራውና ከሥራው ውጪ ለሚደርስበት አደጋ የሕይወት መድን ዋስትና ይገባለታል የተባለ ሲሆን ለአካል ጉዳትና የሕይወት መድን ዋስትና ድርጅቱና ሠራተኛው በጋራ በሚያዋጡት አረቦን ዓመታዊ የህይወት ዋስትና እንደሚገባለት አንቀፁ ይናገራል፡፡

በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና በ2000 ዓ.ም በተደረገው የህብረት ስምምነት መሠረት ለሠራተኞች /ተጠሪን ጨምሮ/ የመድን ዋስትና ገብቶላቸው ተጠሪውም ዓመታዊ አረቦን ማዋጣቱን እያወቀ ለደረሰበት ጉዳት አመልካች ለተጠሪው በገባለት የመድን ሽፋን መሠረት የከፈለውን የጉዳት ካሣ አንሶኛል በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መርምሮ የጉዳት ካሣ በአግባቡ ተከፍሏል በማለት የወሰነውን የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/ለ/ በመጥቀስ ቀሪ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል ሲል የወሰነው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 99288 በቀን 02/05/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16634 በቀን 03/02/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ውሣኔውም የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ስ/ረ